# የኢትዮጵያ አንድነት አርበኞች ግንባር
# (ኢአአግ)
## ETHIOPIAN UNITY PATRIOTS FRONT
## (EUPF)

ETHIOPIAN UNITY PATRIOTS FRONT

አንድ ሀገር
አንድ ሕዝብ
አንድ ሰንደቅ ዓላማና
አንድ የጋራ ዕድል

ONE COUNTRY
ONE PEOPLE
ONE FLAG & ONE
COMMON DESTINY

ቅፅ-004/99 ነሐሴ 01/1999 ዓ/ም

# ከኢትዮጵያ አንድነት አርበኞች ግንባር
# የተሰጠ መግለጫ
# ከጅብ ቆዳ የተሠራ ከራር

የዘመናት አኩሪ ታሪክ ባለቤት ዩሆነችው አገራችን ከትወልድና ከታሪክ ባፈነገጡ አምባገነኖች እጅ ወድቃለች:: ዛሬ ወያኔዉ በዲሞክራሲ ስም እየማለና እየተገዘተ በድርጊት ደግሞ በዘረኝነትና በከፋፋይነት አጀንዳው በመንቀሳቀስ ሕዝባችንን ለከፋ ድህነት፤ለእስራትና፤ለሞት ዳርጓል:: ሕዝባችን መናገር፤የመሰብሰብ፤የመፃፍና በመረጠዉ ወገን የመተዳደር ሰብአዊ መብቶችን ተገፎ በቀየዉ፤በመንደሩና፤በሀገሩ ባይተዋር ሆኖ በመከራና በጨለማ ሕይወት ዉስጥ ይገኛል::

የኢትዮጵያ አንድነት አርበኞች ግንባር (ኢአአግ) ይህን ጨካኝ አገዛዝ አስወግዶ በምትኩ ሕዝባዊና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመገንባት ይልቁንም ደግሞ የሕዝቡን የሥልጣን ባለቤትነት ለማረጋገጥ በፀረ-ወያኔ የአርበኝነት ትግል በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል::በእርግጥ ኢአአግ በእስከ አሁኑ ጉዞው ከቁጥር የሚገባ እርምጃ እየወሰደ ባይሆንም ትግሉ ቀጣይነት ያለዉና የማያቋርጥ ከመሆኑ አንፃር ጊዜ ገዝቶና በአስፈላጊ ሁኔታዎች ሁሉ እራሱን በብቃት አደራጅቶ ትግሉን በፋኖነት ይቀጥላል::ለገባነዉ ቃልኪዳን እዉን መሆንና ላለብን ሀገራዊ ሃላፊነት ቃላችንን ሳናጥፍ በተግባር የምናሳይበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም::

ወያኔዉ የአገዛዝ ዕድሜዉን ለማራዘም ዛሬ በሁለት ሺህ /2000/ ዓመት (አዲስ ዘመን) ስም የአንድነት ሀይሎችን በማባበልና አልያም በሠላማዊ ትግል ስም ለማንበርከክ ደፋ ቀና በማለት ላይ ነዉ::ትናንት ለዘመናት የቆየዉን ታሪካችንን በመቶ (100) ዓመት ገድቦ የኢትዮጵያ ታሪክ የመቶ ዓመት ታሪክ ነዉ እንዳላለን ሁሉ ዛሬ ደግሞ በአንድ ጀምበር አንድ ሺህ ዘጠኝ መቶ /1900/ በመጨመር ሁለት ሺህ ላይ ደርሷል::ከወያኔዉ መሠረታዊ ባሕሪይ አንፃር ይህ ተለዋዋጭነት (የእስስት መልክ) የሚደንቅ ባይሆንም

የዋሆች በዚህ መሠሪ አፍራሽ ፕሮፓጋንዳ በመታለል መጠቀሚያ እንዳይሆኑ ለማሳሰብ ጭምር ነዉ።ይህ የአዲስ ዘመን በዓል ከወያነዉ የሚሰጠን ገፀ-በረከት ሳይሆን የታሪካችን አሻራ፤የማንነታችን መግለጫ እና የኢትዮጵያዊነት ክብር መታወቂያ እንደመሆኑ መጠን ለፍትህና ለዲሞክራሲ የወደቁ ወገኖቻችንን፤ዛሬ በእስራት የሚንገላቱ ወንድሞቻችንንና እህቶቻቸንን እንዲሁም ሀገር አልባ ሆነዉ የተሰደዱ ወገኖቻችንን በማሰብና ስለሀገራችን የወደፊት ዕጣ ፋንታ በማለም ጭምር ልናከብረዉ ይገባል።ከዚህ መለስ ወይም ከዘያ ወዲያ ያለዉና የሚኖረዉ የወያኔ አደንቋሪ ፕሮፓጋንዳ ለጅብ ቆዳ የተሠራ ክራር ቅኝቱ እንብላዉ ከልሆነ በስተቀር ሌላ ፋይዳ የለዉም።

እደሚታወቀዉ የግንቦት 1997 ዓ/ም ሕዝባዊ ምርጫ በወያኔ ብረት አንጋቾች ከተቀለበሰ ወዲህ ይህ ሕዝባዊ ትግል ተመልሶ እንዳያንሠራራ ለማድረግ ወያኔዉ በሙሉ ኃይሉ በመንቀሳቀስ ላይ ነዉ።በተለይም የዲሞክራሲ ሥርዓት አሰፍናለሁ በሚል ቅጥፈት ሕዝባችንን እና የዉጭዉን ዓለም ማህበረሰብ በማደናገር አምባገነንነቱን ለመደበቅ እየጣረ ነዉ።ይህ ዘመቻ የአንድነት ሃይሎች በጋራ እንዳያብሩና እሱ ራሱ በሚያዘጋጀዉ ጨዋታ አዳማቂ በመሆን በሚፈጥራቸዉና በሚያነሳቸዉ የተለያዩ ወቅታዊ ጉዳዩች ብቻ በማተኮር ለመጨረሻዉ የጋራ ግብ ሳይሆን ዉስን በሆኑ የሕዝብ ጥያቄች ዙሪያ ትኩረት አድርገው እዲንቀሳቀሱ ለማድረግ መድረኮችን እያመቻቸ ነዉ። ይህ ደግሞ የተቃዋሚ ሃይሎችን ጊዜ፤ጉልበትና ገንዘብ በማባከን የሕዝባችንን ተስፋ አደብዝዞ ለተጨማሪ አገዛዝ የቀየሰዉ ታላቅ ሴራ ነዉ።በዚህ ረገድ የተቃዋሚዉ ጎራ ይበልጥ አሰላለፉን ለይቶና አንድነቱን በጋራ በማጠናከር ወያኔዉ በፍፁም ሥልጣኑን ወደ ሕዝብ የመመለስ ፍላጎት የሌለዉ መሆኑን በአፅኖት በመረዳት ጭምር የትጥቅ ትግሉን አጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ጥሪያችንን እናቀርባለን።

ዛሬ የተወሰኑ ተቃዋሚ ሓይሎች ከእስር መፈታት በሀገር ዉስጥና በውጭ የሚኖረዉ ኢትዩጵያዊ የትግል ዉጤት መሆኑ ባያጠያይቅም አሁን ድረስ ታስረዉ ፍዳቸዉን የሚያዩት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ወገኖቻችን ዕጣ ፋንታም ገና ምላሽ አላገኘም።የታሠረዉ በጠቅላላ የአንድ ትወልድ ሕዝብ በመሆኑ ሕዝቡ በመላ ነፃ መዉጣት አለበት።ወያኔዉ ሲያሻዉ የሚገድል፤ሲፈልግ የሚያስርና የሚፈታ በመሆኑ እራሱን የዲሞክራሲ ተዋናይ ወይም እርቅ ፈላጊ እንደሆነ አድርጎ ለመቅረብ ይሞክራል።ይህን የመሆን ሳይሆን የመምሰል የወያኔ ባሕሪይ አንዳንዶቹ በአግባቡ መመዘን ተስኖአቸዉ የሀገራችን ችግር መፍትሄ እንዳገኛና ወያነዉ በፈጠረዉ የዲሞክራሲ መንገድ ብቻ ጠቀሜታ ሊገኝ እንደሚችል የአቀባባይነት ርካሽ ተልዕኮአቸዉን በመርጨት ላይ ይገኛሉ። በእርግጥ ለሆዳቸዉ ያደሩ ባንዳዎች ከሆዳቸዉ ያለፈ ራዕይ ስለሌላቸዉ አብረዉ ቢዘፍኑ

አይደንቅም፡፡እነዚህ ሃይሎች ይህ ለሕዝባችን ዛሬ የጨለመዉ ጊዜ ነገ በንጋት ሲለወጥ ለሕዝብና ለታሪክ ፍርድ መቅረባቸዉ አይቀሬ ነዉ፡፡

የኢትዮጵያ አንድነት አርበኞች ግንባር (ኢአአግ) አምባገነኑ የወያኔ የአገዛዝ ሥርዓት እጁን በሠላማዊ መንገድ ይሠጣል ብሎ ስለማያምን የትጥቅ ትግሉን አጠናክሮ ይቀጥላል፡፡በሀገር ዉስጥና በዉጪ ሀገር የምትገኙ የግንባሩ አስተባባሪች፤አባላትና ደጋፊ-ች የጀመራችሁትን ሁለገብ የአርበኝነት ትግል አጠናክራችሁ እንድትቀጥሉ እናሳስባለን፡፡

ሠልፍ የጀግና ድል የእግዚአብሔር ነዉ!
ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!

እሱባለዉ ጫኔ
የኢትዮጵያ አንድነት አርበኞች ግንባር (ኢአአግ)
ቃል አቀባይ